
የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የጤና ባለሙያዎች
# የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያ



ጥቅምት 2011 ዓ.ም.

# የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የጤና ባለሙያዎች
# የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ
# መመሪያ

ህዳር 2011ዓ.ም.

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

አጠቃላይ ........ 1

1. ርዕስ ........ 1
2. ትርጓሜ ........ 1
3. የተፈጻሚነት ወሰን ........ 2
4. መርህ ........ 3

ክፍል ሁለት ........ 4

ተግባር እና ኃላፊነት ........ 4

5. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ........ 4
6. የክልል ጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካል ........ 6
7. እውቅና ሰጪዎች ........ 6
8. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ........ 9
9. የሙያ ማህበራት ........ 11
10. የጤና ባለሙያዎች ........ 12
11. አሰሪዎች ........ 13
12. አጋር ድርጅቶች ........ 13

ክፍል ሦስት ........ 14

እውቅና ስለመስጠት፣ የመለኪያ አሰጣጥና መስፈርቶች ........ 14

13. ለእውቅና ሰጪነት እውቅና ስለማግኘት ........ 14
14. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ እውቅና አሰጣጥ ... 14
15. ኮርስን ስለማጽደቅ ........ 15
16. የክሬዲት አሰጣጥ እና መስፈርቶች ........ 16

ክፍል አራት ........ 17

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 17

17. የጥቅም ግጭት ........ 17
18. የቅሬታ አያያዝ ........ 17
19. ያልተካተቱ ጉዳዮች ........ 17
20. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች ........ 17
21. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ........ 17

# መግቢያ

በጊዜ ሂደት እየተለወጠ ካለው የህክምና እውቀት፣ የቴክኖሎጅ እድገት፣ ፈጣን ተቋማዊ ለውጥ፣ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ፍላጎት እና ተጠያቂነት ጋር አብሮ ለመሄድ ሙያዊ ብቃትን ማሳደግ አስፈላጊ ስለሆነ፤

ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ የጤና ባለሙያዎችን ብቃት ለማሳደግ እንዲሁም የጤና አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ስለሚረዳ፤

በኢትዮጵያ ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ የተለያዩ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስራዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጤና ሙያ ስራ ፈቃድን ለማደስ በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ከተቀመጡ መስፈርቶች ውስጥ ተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ዋነኛው የቁጥጥር መስፈርት በመሆኑ፤

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ባገኘው ውክልና በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ አንቀጽ 55 (3) እና በምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ አንቀጽ 66 (1) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

### 1. ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያ" ቁጥር ---/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 2 ስር ለተቀመጡ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ እና የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ"** ማለት የጤና ባለሙያዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ፣ በብቃትና በተሰጣቸው ህጋዊ የስራ ወሰን ውስጥ በሙያቸው እንዲያገለግሉ በስራ ዘርፋቸው የሙያ ብቃታቸውን የሚጠብቁበትና የሚያሳድጉበት የተለያዩ የትምህርት ተግባራትን ያከተተ ነው፤
2. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ማለት ነው፤
3. **"ሚኒስቴር"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ማለት ነው፤
4. **"የጤና ባለሙያ"** ማለት በጤና ጥበቃ ወይም በክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካል ፈቃድ የተሰጠው የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ የማከምና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን የሚያከናውን የጤና ሰራተኛ ነው፣

5. **"እውቅና"** ማለት የጥራት ማረጋገጥ ሂደት ዓይነት ሲሆን ተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎች እና የትምህርት ፕሮግራሞች በእውቅና ሰጪ አካል የሚገመገምበት አሰራር ነው፤
6. **"የተከታታይ ትምህርት መለኪያ"** ማለት በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ውስጥ አንድ የመማሪያ ተግባር ለመለካት የሚሰጥ ተጓዳኝ ነጥብ ነው፤
7. **"እውቅና ሰጪ"** ማለት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎችን እና የትምህርት ፕሮግራሞችን እውቅና የሚሰጡ በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጣቸው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ወይም የጤና ሙያ ማህበራት ነው፤
8. **"ተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎች"** ማለት በእውቅና ሰጪ አካል እውቅና የተሰጣቸው ዩኒቨርሲቲዎች፣ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች፣ የሙያ ማህበራት፣ ሆስፒታሎች እና ስልጠናን በመስጠት ልምድ ያላቸው ሌሎች የአማካሪ ድርጅቶች እና መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት የሚሰጡ የግል ወይም የመንግስት ተቋማት ነው፤
9. **"አሰሪ"** ማለት የጤና ባለሙያን በሙያው እንዲሰራ የቀጠረ ማንኛውም ድርጅት ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በጤና ሙያ ላይ በተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች፣ እውቅና ሰጪና የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. መርህ

1. የማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጠውን የተከታታይ ትምህርት መመዘኛዎችን ሳያሟላ ሊታደስ አይችልም፡፡
2. በእውቅና ሰጪ አካል እውቅና ያልተሰጠውና በሚኒስቴሩ ያልጸደቀ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ ዋጋ አይኖረውም፡፡
3. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ጋይድላይን መሰረት የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ደረጃውን እንዲጠብቅ ይደረጋል፡፡
4. የጤና ባለሙያዎችና ታካሚዎች ወይም ደንበኞች ከህይወት ዘመን ትምህርት የሚያገኙትን ጥቅሞች ታሳቢ በማድረግ የጤና ባለሙያዎች የሚጠበቅባቸውን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መስፈርቶች ለማሟላት ይሰራሉ፡፡
5. እውቅና ሰጪ አካላትና የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎች የሙያ ስነ-ምግባር እንዲተገበር የሙያ ማህበራትን ያበረታታሉ፡፡

# ክፍል ሁለት

## ተግባር እና ኃላፊነት

### 5. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ሚኒስቴሩ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ ከክልል ጤና ቢሮ፣ ከክልል ተቆጣጣሪ አካላት፣ እውቅና ሰጪ ከሆነ ወይም የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ከሆኑ የሙያ ማህበራት፣ ከስልጠና ተቋማትና ከአጋር ድርጅቶች የተውጣጣ 16 አባላት ያሉት የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) ያቋቁማል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሰረት የተቋቋመው ኮሚቴ ከአባላቱ መካከል በተመረጠ ሊቀ-መንበር የሚመራ ሲሆን ፀሀፊው ከሚኒስቴሩ የሚወከል ይሆናል፡፡
3. ኮሚቴው የራሱን የአሰራር ሕግና ደንብ ያወጣል፡፡
4. ኮሚቴው የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ/ የማስፈጸሚያ ጋይድላይንና ማኑዋል ያዘጋጃል፤
   ለ/ ተፈጻሚነት ባለው ጋይድላይን መስፈርት መሰረት ለእውቅና ሰጪዎች እውቅና ይሰጣል፤
   ሐ/ ቅሬታን በመመርመር በእውቅና ሰጪና በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ላይ አግባብነት ያለው አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፤
   መ/ እንደአስፈላጊነቱ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ጋይድላይንን ይከልሳል፤
   ሠ/ በእውቅና ሰጪዎች ላይ የጥራት ቁጥጥር ያካሂዳል፡፡ በጥራት ቁጥጥር ስራው መሰረት መሰረታዊ የሆነ ጉድለት ለሚኒስቴሩ ከተጠቆመ የእውቅና ሰጪነት ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፤
5. ጤና ባለሙያዎችን በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ትምህርት ለመመዝገብ የተቋማዊ እውቅና አሰጣጥ ስርዓትን ይዘረጋል፤

6. እውቅና ያገኙ እውቅና ሰጪዎችንና የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎችን የጤና ባለሙያዎች እንዲያውቋቸውና ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያሳውቅበትን ስርዓት ይዘረጋል፤
7. ተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓቱን ይመራል፤ ስርአቱን በገንዘብ ለመደገፍ እና ለማስቀጠል ስልቶችን ይቀይሳል፡፡
8. የሚኒስቴሩ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ቡድን የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ/ ተከታታይ ሙያ ማጎልበቻን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ቅጾችን ያዘጋጃል፤ ያቀርባል፤
   ለ/ ከበይነ-መረብ የሚወርድ የኤሌክትሮኒክ መመሪያ፣ ቅጽ፣ ተያያዥ የሰነዶች ቅጅ፣ እውቅና የተሰጣቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎችን እና የኮርሶች ዝርዝርን የያዘ ወቅታዊ የሆነ ድረ-ገጽን ይይዛል፤
   ሐ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የመረጃ ቋት ያዘጋጃል፤ ይይዛል፤
   መ/ የእውቅና ሰጪዎችን እና እውቅና የተሰጣቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎችን ዝርዝር ወቅቱን ጠብቆ ያሳውቃል፤
   ሠ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሀገራዊ አፈጻጸምን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤
   ረ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርሶች በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ጋይድላይን መሰረት መሰጠታቸውን ያረጋግጣል፤
   ሰ/ በእውቅና ሰጪ አካላት ለተከታታይ ትምህርት የተሰጡ መለኪያዎችን አግባብነት ይፈትሻል፤
   ሸ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሀገራዊ አፈጻጸምን ይቆጣጠራል፤
   ቀ/ የክልል ተቆጣጣሪ አካላትንና የክልል ጤና ቢሮዎችን አቅም ለማሳደግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 6. የክልል ጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካል

የክልል ጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካል፡-

1. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ቡድንና ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤
2. በክልሉ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ የፍላጎት ጥናት እንዲካሄድ ያስተባብራል፤
3. በክልሉ የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ትምህርትን ይደግፋል፤ያመቻቻል፤
4. በክልሉ የጤና ባለሙያዎች የስራ ላይ ስልጠናና የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስራዎችን ለመደገፍ ሀብት ያሰባስባል፤
5. በእውቅና ሰጪ ወይም በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ተቋማት ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል፤
6. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የመረጃ ቋት ያዘጋጃል፤ ይይዛል፡፡

## 7. እውቅና ሰጪዎች

1. እውቅና ሰጪ መሆን የሚፈልጉ ተቋማት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፡፡ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ ነባር እውቅና ሰጪዎችን በመመርመር ለእውቅና ሰጪዎች ለተጨማሪ ሶስት ዓመታት የሚጸና ፍቃድ ይሰጣል፡፡ እውቅና ሰጪው መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ ፍቃዱ ከሶስት አመት በኋላ እንደገና ይታደሳል፡፡
2. የእውቅና ሰጪ ሃላፊነቶች፡-

   ሀ/ ለተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪነት እና ኮርሶች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይገመግማል፤

   ለ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ጋይድላይን ተፈጻሚነትን ይከታተላል፤

ሐ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪው ተፈጻሚነት ያላቸውን የሚኒስቴሩን ደንብ እና መመሪያ ሳይከተል ሲቀር የተሰጠውን የተከታታይ ትምህርት መለኪያን ይከልሳል፤

መ/ የሚከተሉትን ተግባሮች በመጥቀስ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎችን በየዓመቱ በመገምገምና በመመዘን ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

- በየዓመቱ የተከናወኑ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ተግባራት ዝርዝር፤
- የሁሉም የቀረቡ ማመልከቻዎች መረጃና ውጤታቸው፣ (ይህ መረጃ ቢያንስ ለ5 ዓመታት መቀመጥ ይኖርበታል)
- ሁሉም የስነ-ምግባር ተግባራት፤
- ተግባራቱ ከባለሙያው የስራ ዘርፍ ጋር ያለው አግባብነት፤
- ተግባሩ ከአንድ ጊዜ በላይ ለተመሳሳይ ተሳታፊ የተሰጠ ስለመሆኑ፤ እና
- ማንኛውም ያጋጠመ ተግዳሮት፡፡

ሠ/ በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎች ላይ የሚቀርብን ቅሬታ ይመረምራል፤ አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፤

ረ/ እውቅና ለተሰጣቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት መረጃዎች መለያ በመስጠት በድረ-ገጽ ላይ እንዲገባና እንዲጫን ለሚኒስቴሩ ይሰጣል፤

3. የጤና ሳይንስ ትምህርት የሚሰጡ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችና መስፈርቶችን የሚያሟሉ የጤና ሙያ ማህበራት እውቅና ሰጪ ይሆናሉ፡፡
4. እውቅና ሰጪ የሚሆን ተቋም የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-የኢንተርኔት አገልግሎት፤ ዳታ ቤዝ ያለው

ኮምፒዩተር፣ ኢ-ሜይል፣ ፋክስና ለዚህ ተግባር የተመደበ የቢሮ አስተዳደር ረዳት፡፡

5. እውቅና ሰጪው ተቋም የእውቅና ሰጪ ዳይሬክተር፣ የቢሮ ረዳት/ጸሀፊ እና የሙሉ ጊዜ ወይም የትርፍ ጊዜ ሰራተኛ የሆኑ ቢያንስ 5 አባላት ያሉት የባለሙያዎች ፓናል ሊኖረው ይገባል፡፡
6. የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ የእውቅና ሰጪ ኮሚቴ አባላት ተገቢ ያልሆነ አሰራርን በሚመለከት የተቀመጡትን የስነ-ምግባር ደንቦችና ፖሊሲዎች መከተል አለባቸው፡፡
7. የእውቅና ሰጪ ለእውቅና ፈቃድ የሚቀርብ የሙያ ማጎልበቻ ተግባር ከንግድ ተፅዕኖ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ለእውቅና ፈቃድ የሚቀርብ የሙያ ማጎልበቻ ተግባር ስነ-ምግባርን የጠበቀ፣ አስተማሪ የሆነ፣ ሚዛናዊ የሆነ አስተያየት ያለውና ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ለፕሮሞሽን የማይውል መሆን አለበት፡፡
8. ውይይት የማያስፈልገው እና ውስብስብ ያልሆነ ማመልከቻ ሲኖር የተሠጠው የተከታታይ ትምህርት መለኪያ በተመደበው ሰው በኮሚቴው መጪ መደበኛ ስብሰባ ላይ በግልፅ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡ ይሁን እንጂ እውቅና ሰጪው የቀረበው የሙያ ማጎልበቻ ተግባር ከንግድ ተፅዕኖ ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም የሙያ ማጎልበቻ ተግባሩ ስነ-ምግባርን የጠበቀ፣ አስተማሪ የሆነ፣ ሚዛናዊ የሆነ አስተያየት ያለው እና ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ለፕሮሞሽን የማይውል መሆን አለበት፡፡
9. ማመልከቻው አወዛጋቢ ሲሆን እና ስልጣን የተሰጠው ኮሚቴ ውሳኔ ላይ መድረስ ሳይችል ሲቀር (ወይም በሙያ ማጎልበቻ አቅራቢ ይግባኝ ከተባለ) ማመልከቻው ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ለውሳኔ ለሚኒስቴሩ ይቀርባል፡፡

10. ለተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪነትና የተግባራት ዕውቅና ለማግኘት የሚከፈል ክፍያ በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ በጸደቀ ጋይድላይን መሰረት ይሆናል፡፡
11. እውቅና ለመስጠት የሚከፈል ክፍያን የሚመለከተው ጋይድላይን በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ የሚጸድቅ ሆኖ በየዓመቱ ኦዲት ይደረጋል፡፡
12. የሚኒስቴሩ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ የእውቅና ሰጪዎችን አሰራር በሚመለከት የጥራት ማረጋገጥ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ በጥራት ቁጥጥር ስራው መሰረት መሰረታዊ የሆነ ጉድለት ለሚኒስቴሩ ከተጠቆመ የእውቅና ሰጪነቱን እንደገና በመመርመር ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
13. እውቅና ሰጪ የሆነ አካል ራሱ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ መሆን ሲፈልግ እውቅና የሚያገኘው ከሌላ እውቅና ሰጪ አካል ይሆናል፡፡
14. እውቅና ሰጪ በአቅራቢው የተሰጠውን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡

## 8. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ

የሙያ ማጎልበቻ ሰጪ፡-

1. ሰልጣኞች ላይ ሊያመጣ ያሰበውን ብቃት፣ የስራ አፈፃፀም፣ በታካሚ ጤና ላይ የሚመጣውን ለውጥ የሚገልፅ የፕሮግራሙ ተልዕኮ ይኖረዋል፡፡
2. እውቅና ለማግኘት ሙሉ ለሙሉ የተሞላ ቅጽ አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶችና ክፍያ ጋር ለእውቅና ሰጪው አካል ያቀርባል፡፡
3. እያንዳንዱን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስልጠና ከመሰጠቱ 3 ወር በፊት ለግምገማና ፈቃድ ለማግኘት ለእውቅና ሰጪው አካል መቅረብ አለበት፡፡

4. የይዘት፣ የፕሮግራምና የትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ባለሙያዎችን (instructional design experts) ያካተተ የኤክስፐርቶች ፓናል ይሰይማል፡፡
5. የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-
   ሀ/ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ዳይሬክተር/አስተባባሪ (ቢያንስ በጤና ሳይንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው)፤ የስልጠና ባለሙያ፤ የመረጃና ቴክኖሎጅ ባለሙያ፤ እና የቢሮ ረዳት/ጸሀፊ፤
   ለ/ የኢንተርኔት አገልግሎት፣ ሀገራዊ የስልጠና መረጃ ሶፍትዌር የመረጃ ቋት እና የስልክ አገልግሎት ያለው ቢሮ፤
   ሐ/ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻን ፊት ለፊት ለመስጠት የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ የስልጠና አዳራሽ እና አነስተኛ የቡድን ውይይት ማካሄጃ ክፍሎች፤ እና
   መ/ ኮምፒዩተር (ዴስክቶት/ላፕቶፕ)፤ ማተሚያ፣ ኤል ሲዲ፣ እና የፎቶ ኮፒ ማሽን፤
6. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ ያዘጋጃል፤ እውቅና ሲሰጠውም ኮርሶቹን ይሰጣል፤
7. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻን ኮርስ ከማዘጋጀቱ በፊት በዘርፉ እውቅና የተሰጠው ተመሳሳይ ሰነድ ስለመኖሩ ያረጋግጣል፤
8. ለዕውቅና የሚቀርብ ኮርስ ቀድሞ እንደ ሀገራዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ እውቅና ካልተሰጠው በስተቀር ለአንድ ኮርስ ኮድ እንዲሁም ደግሞ እውቅና የሚሰጠው ለአንድ አቅራቢ ብቻ ይሆናል፡፡
9. በኮርስ ዝግጅትና አሰጣጥ ወቅት ተፈጻሚነት ያላቸውን የጥራት መስፈርቶች ያሟላል፤
10. ለእያንዳንዱ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባር የውስጥ የክትትልና ግምገማ ውጤት ሪፖርት በሰነድ ይይዛል፤ ያቀርባል፤

11. የታቀዱ ዓመታዊ ተግባራትን ከተጓዳኝ የእውቅና መለያ ቁጥር እና የተከታታይ የትምህርት መለኪያው ጋር በማድረግ ይፋ ያደርጋል፡፡
12. ለአፈጻጸም የኦዲት ስራ እንዲያግዝ የሙሉ ጊዜ የተሳታፊዎች የተሳትፎ መከታተያ ሰነድ መረጃ ኩነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ለአምስት አመታት ያህል ይይዛል፡፡
13. አመታዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራትን በሚመለከት ለሚኒስቴሩና ለእውቅና ሰጪው ሪፖርት ያደርጋል፤
14. እንደአስፈላጊነቱ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርሶችን ይከልሳል፤ እንዲጸድቅለትም ያመለክታል፤
15. ፍቃዱን በየዓመቱ ለማሳደስ ያመለክታል፤
16. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በሚታይ ቦታ ያስቀምጣል፡፡

## 9. የሙያ ማህበራት

ሀ/ መስፈርቶችን ካሟሉ እውቅና ሰጪ እንዲሁም ደግሞ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ለ/ ተገቢነት ላለው የሙያ ዘርፍ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መለኪያ ነጥብን በተመለከተ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ሐ/ እንደተገቢነቱ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳሉ፤ ሊሰጡ የሚገቡ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራትን በሚመለከት ምክረ-ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

መ/ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ባለሙያዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ የሚበረታቱበትን ስልቶች ይቀይሳሉ፡፡

## 10.የጤና ባለሙያዎች

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-
   ሀ/ የተግባሩን ወይም የኮርሱን አስተማሪነት እንዲሁም ከትምህርቱ አስፈላጊነት አንጻር አግባብነቱን ይገመግማል፡፡
   ለ/ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮርሱን ከመውሰዳቸው በፊት የአቅራቢውን ህጋዊነት ያረጋግጣል፡፡
   ሐ/ የሚጠበቅባቸውን ዓመታዊ የተከታታይ የትምህርት መለኪያ ይወስዳሉ፤፤
   መ/ ለሚወስዱት ለእያንዳንዱ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባር የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፤ ቢያንስ ለሶስት ዓመትም ሰነዱን ይይዛሉ፤
2. ከአንድ በላይ ባሉ የሙያ ዘርፎች የተመዘገበ የጤና ባለሙያ ለእያንዳንዱ ለተመዘገበበት የሙያ ዘርፍ የተከታታይ የትምህርት መለኪያ መውሰድ አለበት፡፡
3. አንድ ባለሙያ ከአንድ በላይ የሙያ ዘርፎች ካሉት በአንድ አግባብ የሆነ የተከታታይ የትምህርት ተግባር (Cross cutting subjects) ላይ ያገኘው የተከታታይ የትምህርት መለኪያ ለሌላኛውም ሙያ አግባብነት ካለው ለሁለቱም የሙያ ዘርፎች ሊወሰድለት ይችላል፤
4. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት ላይ ለመሳተፉ ስልቶችን ይለያል፤
5. የራሳቸውን የትምህርት ፍላጎት በመለየት ለሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይችላሉ፤
6. የጤና ባለሙያዎች አግባብ ላለው የሚኒስቴሩ ወይም ለክልል የጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካል በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ አሰጣጥ እና የስልጠና ጥራት ላይ ያላቸውን ቅሬታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፤

## 11.አሰሪዎች

አሰሪዎች፡-

1. የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ፕሮግራምን ከጤና ባለሙያዎች ዓመታዊ የአፈጻጸም ግምገማ ጋር ያስተሳስራሉ፤
2. ለሰራተኞቻቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የሚሰጥበትን ጊዜ የጊዜ ሰሌዳቸው ውስጥ ያካትታሉ፤፤ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና የተሳተፉ ሰራተኞችን በሚመለከት ዓመታዊ ሪፖረት ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፤
3. ከሚኒስቴሩ፣ ከክልል የጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካል እና ከተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሰጪዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻን የሚመለከትን መረጃ በወቅቱ ለሰራተኞቻቸው ያሳውቃሉ፡፡
4. ለጤና ባለሙያዎቻቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያከናውናሉ፤ እንደ አስፈላጊነቱ ባለሙያዎቹን ያግዛሉ፤
5. ሰራተኞቻቸው በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፉ በቂ ጊዜ ይሰጣሉ፤
6. ሰራተኞቻቸው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ያግዛሉ፤

## 12.አጋር ድርጅቶች

- የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓቱ ስኬታማ እንዲሆን ለሚኒስቴሩ፣ ለክልል የጤና ቢሮ/ተቆጣጣሪ አካል እና ለመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡
- የሙያ ማህበራት በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓቱ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

# ክፍል ሦስት

## እውቅና ስለመስጠት፣ የመለኪያ አሰጣጥና መስፈርቶች

## 13.ለእውቅና ሰጪነት እውቅና ስለማግኘት

1. የዚህን መመሪያ እና ተፈጻሚነት ያላቸው ጋይድላይኖችን መስፈርት የሚያሟላ እውቅና ሰጪ ለመሆን የሚፈልግ አመልካች ለሚኒስቴሩ ሊያመለክት ይችላል፤
2. ለእውቅ ሰጪነት የሚያመለክት አካል በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ማስፈጸሚያ ጋይድላይን መሰረት የሚጠይቀውን የሰው ሀይልና የመሰረተ-ልማት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤
3. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1 እና 2) መሰረት የቀረበ ማመልከቻን ከቀረበው ማስረጃ አንጻር በመገምገም ሊያጸድቅ፣ የማስተካከያ ምክረ-ሀሳብ ሊሰጥ ወይም ማመልከቻውን ሊከለክልስ ውድቅ ሊደርገው ይችላል፤
4. የእውቅና ሰጪነት ፈቃድ ለሶስት ዓመት የሚፀና ይሆናል፤
5. የማመልከቻ ሰነዶች፣ የማመልከቻው ውሳኔና የፓናሉ ቃለ ጉባኤ ቢያንስ ለአምስት አመታት መያዝ ይኖርበታል፤
6. የእውቅና ሰጪነት ፈቃድ የምስክር ወረቀት በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ሲሆን እውቅና ጠያቂው የፈቃድ ዘመኑ ከማለቁ 2 ወራቶች በፊት ፈቃዱ እንዲታደስለት ማመልከት አለበት፡፡

## 14.የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ እውቅና አሰጣጥ

1. የዚህን መመሪያ እና ተፈጻሚነት ያላቸው ጋይድላይኖችን መስፈርት የሚያሟላ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ለመሆን የሚፈልግ አመልካች ለእውቅና ሰጪ አካል ሊያመለክት ይችላል፤
2. ለተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪነት የሚያመለክት ማንኛውም አካል በተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማስፈጸሚያ ጋይድላይን የሚጠይቀውን የሰው ሀይልና መሰረተ-ልማት

መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

3. እውቅ ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1 እና 2) መሰረት የቀረበ ማመልከቻን ከቀረበው ማስረጃ አንጻር በመገምገም ሊያጸድቅ፣ የማስተካከያ ምክረ-ሀሳብ ሊሰጥ ወይም ማመልከቻውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፤
4. የተሰጠው ፈቃድ ለአንድ አመት የሚጸና ይሆናል፤
5. የማመልከቻ ሰነድ እንዲሁም የማመልከቻው ውሳኔና የፓናሉን ቃለ ጉባኤ ቢያንስ ለአምስት አመታት መያዝ ይኖርበታል፡፡
6. ለተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪነት ፈቃድ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው እውቅና ሰጪው ሲሆን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪው የፈቃድ ዘመኑ ከማለቁ 2 ወራቶች በፊት ፈቃዱ እንዲታደስለት ማመልከት አለበት፡፡

## 15.ኮርስን ስለማጽደቅ

1. ኮርስ ማጸደቅ የሚፈልግ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢ ስልጠና ለመስጠት ካሰበበት ቀን ቢያንስ ከ3 ወር በፊት ፈቃድ ለማግኘት ለእውቅና ሰጪው ማመልከት አለበት፡፡
2. እውቅና ሰጪው የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ጋይድላይኑን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የማመልከቻውን ሙሉነት ያረጋግጣል፤ የማመልከቻ ቁጥርና የሙያ ምድብ ይሰጣል፡፡
3. እውቅና ሰጪው በአንቀጽ 15 ንዑስ-አንቀጽ 2 መሰረት በቀረበው ማመልከቻ ኮርሱንና በአቅራቢው ለኮርሱ የተጠየቀውን ክሬዲት ሊያጸድቅ፣ የማስተካከያ ምክረ-ሀሳብ ሊሰጥ ወይም ማመልከቻውን ሊከለክል የሚችል ሆኖ ውሳኔውን በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ያሳውቃል፡፡

## 16.የክሬዲት አሰጣጥ እና መስፈርቶች

1. ለተወሰደ ኮርስ ክሬዲት ሊያዝ የሚችለው እውቅና ሰጪው አካል ኮርሱን ካጸደቀው እና ኮርሱ ከአመልካቹ ወቅታዊ የስራ ዘርፍ አንጻር ጠቃሚ ከሆነ ብቻ ነው፡፡
2. የማንኛውም የጤና ባለሙያ የስራ ፈቃድ የሚታደሰው በዓመት 30 ክሬዲት እና በሶስት አመት 90 ክሬዲት ካገኘ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) ቢኖርም የሙያ ማህበራት አግባብ ላለው የሙያ ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ ክሬዲት እንዲጠየቅ ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
4. ከውጭ ሀገር ከተገኘ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባር ወይም ኮርስ የክሬዲት አያያዝ ተፈጻሚነት ባለው ጋይድላይን መሰረት ይሆናል፡፡
5. ለአንድ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ ሊያዝ የሚችለው ከፍተኛ ክሬዲት ከ15 መብለጥ የለበትም፡፡
6. ከአንድ ከተወሰደ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት የሚያገለግለው በአንድ የሙያ ስራ ፍቃድ ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡
7. በአንድ ዓመት ውስጥ የተገኘ ሙያ ማጎልበቻ ክሬዲት ወደ ሌላ የበጀት ዓመት ሊሸጋገር አይችልም፡፡
8. አንድ አሰልጣኝ በአንድ የሙያ ስራ ፍቃድ ጊዜ ውስጥ አንድን ኮርስ ከአንድ ጊዜ በላይ ቢሰጥ የሚያገኘው ክሬዲት ከአንድ ጊዜ በላይ አይቆጠርለትም፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17.የጥቅም ግጭት

ማንኛውም ዓይነት የጥቅም ግጭት በሚኒስቴሩ ወይም በክልል የጤና ቢሮ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

### 18.የቅሬታ አያያዝ

ሀ. ቅሬታዎች ለሚኒስቴሩ ወይም ለክልል ጤና ቢሮ ይቀርባሉ፡፡ ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ጤና ቢሮ ደግሞ የቀረበውን ቅሬታ ለተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

ለ. የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ አግባብነት ያላቸውን የእርምጃዎች ምክረ-ሀሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለሰው ልማት ሃብት ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

### 19.ያልተካተቱ ጉዳዮች

የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻን በሚመለከት በዚህ መመሪያ ያልተካተተ ማንኛውም ተያያዥ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ባወጣው ጋይድላይን የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 20.ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 21.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡



**ዶ/ር አሚር አማን**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚንስትር**

**ህዳር 2011 ዓ.ም**